*ይዘቶች*

1 **መግቢያ** ..... 3
2 **አቅራቢ የስራ ጤና እና ደህንነት መስፈርቶች** ..... 3
3 **የኤሪክሰን የ OHS አሰራር ደረጃ** ..... 3
4 **የኤሪክሰን ልዩ የ OHS ደረጃዎች** ..... 4
5 **የለውጥ መረጃ** ..... 4

© Ericsson AB 2022

መብቱ የተጠበቀ ነው። በዚህ ሰነድ ውስጥ ያለው መረጃ የኤሪክሰን ነው እናም ያለ ማሳወቂያ ሊቀየር ይችላል።
ኤሪክሰን ለማንኛውም የእውነታ ትክክል አለመሆን እና የህትመት ስህተት ሀላፊነት አይወስድም።

## 1 መግቢያ

ኤሪክሰን በተቀናጀ ቡድን አቀፍ የጤና እና የደህንነት አቀራረብ ፤ ለሁሉም ጤናማ እና ደህንነቱ የተጠበቀ የስራ ከባቢ ለመፍጠር ይተጋል፡፡

ደህንነቱ የተጠበቀ እና ጤናማ የስራ ከባቢ ለሁሉም ሰራተኛ በአለም አቀፍ ደረጃ ማረጋገጥ ኤሪክሰን በአፅንኦት ሚሰራበት ቁርጠኛ አቋሙ ነው፡፡ ኤሪክሰን እዚህ ቁርጠኝነቱ ላይ አቅራቢዎቹን እና ሰራተኞቹንም ያካትታል፡፡

ኤሪክሰን በስራ ቦታ ላይ በመሰረታዊ ሰብአዊ መብቶች፣ጉልበት፣ የደህንነት እና ጤና ደረጃዎች ፣ የአካባቢ አስተዳደር እና ፀረ-ሙስና ዙርያ ለሁሉም አቅራቢዎች የስነ-ምግባር ደንብ አውጥቷል፡፡ ይህ ሰነድ በአቅራቢዎቻችን ላይ የምናስቀምጠውን የስራ ቦታ ጤንነት እና ደህንነት ግዴታዎችን (OHS) ያብራራል፡፡ የዚህ OHS አፈፃፀም በአቅራቢዎች ቁጥጥር እና ግምገማ የሚመዘን ይሆናል ፡፡

የኤሪክሰንን የስነ-ምግባር ደንብ እና የአቅራቢዎችን የ OHS ግዴታዎችን በበይነ መረብ ለማግኘት ከዚህ በታች ያለውን ማስፈንጠሪያ ይጎብኙ፦

http://www.ericsson.com/responsible-sourcing

## 2 አቅራቢ የስራ ጤና እና ደህንነት መስፈርቶች

ኤሪክሰን አቅራቢዎቻችን ቢያንስ ከዚህ በታች ያሉትን ግዴታዎች የሚያሟላ የራሳቸው የ OHS አስተዳደረር ስርአት እንዲኖራቸው ያስገድዳል፦

**OHS ፖሊሲ፦** አቅራቢው የ OHS ፖሊሲ ሊኖረው ይገባል፡፡ ፖሊሲው የአቅራቢውን የ OHS አደጋዎች ተፈጥሮ እና ልክ ያገናዘበ እንዲሁም ጉዳትን እና ህመምን ለመከላከል እና ለቀጣይነት ላለው መሻሻል ቁርጠኝነትን ያካተተ መሆን አለበት፡፡

**የአደጋ ግምገማ፦** አቅራቢው የራሱን OHS አደጋዎች መለየት እና መመዝገብ ያለበት ሲሆን አስፈላጊውን መቆጣጠሪያም መለየት አለበት፡፡

**የማሻሻያ መርሃ-ግብር፦** አቅራቢው የ OHS የማሻሻያ መርሃ-ግብር ሊኖረው ይገባል፤ ይህም ግብ እና የተግባር እቅድ ሊያካትት ይገባል፡፡

**ህግ ማውጣት፦** አቅራቢው ተግባራዊነት ላላቸው የ OHS ህጎች እና ደንቦች ተገዢ ሊሆን ይገባል፡፡

በአካባቢው የOHS ህግ ወይም ደንቦች እና ኤሪክሰን ግሎባል ኦኤችኤስ መመዘኛዎች እና በአቅራቢው ላይ በዚህ ሰነድ መካከል ግጭት ሲፈጠር በጣም ጥብቅ የሆኑት (ዎች) ተፈጻሚ ይሆናሉ (በሚመለከተው የግዴታ OHS ህግ ወይም ደንቦች ካልተፈቀደ በስተቀር)

**ብቁነት፦** አቅራቢው ሁሉም ሰራተኞች በተመደቡበት ስራ ብቁ መሆናቸውን፤ ተገቢው ትምህርት፣ስልጠና እና ልምድ እንዳላቸው ማረጋገጥ አለበት፡፡

**ዘገባ እና ምርመራ፦** አቅራቢው አግባብነት ያለው የክስተቶች ዘገባ እና ምርመራ ሊኖረው ይገባል፤ ይህም የእርምት እርምጃ ሒደትን ያካተተ መሆን አለበት፡፡

## 3 የኤሪክሰን የ OHS አሰራር ደረጃ

በሚቻልበት ጊዜ፤ የአቅራቢዎች የ OHS አስተዳደር ስርኣት ከዚህ በታች ከተጠቀሱት የኤሪክሰን ግሩፕ የ OHS አሰራር ደረጃዎች ግዴታዎች ቢያንስ ትንሹን ግዴታ ማሟላት ወይም ከተቀመጡት በላይ ማሟላት አለበት፦

- የኬሚካል አያያዝ፤
- ከፍታ ላይ መውጣት እና መስራት፤
- የተወሰነ ስፍራ ግቤት፤
- የግንባታ እና ሲቪል ስራ አስተዳደር፤
- የአሽከርካሪ እና ተሽከርካሪ ደህንነት፤
- ከባቢያዊ እና የስራ ቦታ ሁካታ ፤
- ለሬዲዮ ሞገድ ኤሌክትሮማግኔቲክ ተጋላጭነት ፤
- እሳት መከላከል፤
- ለብቻ መስራት፤
- የእቃ አሰራር መመሪያ አያያዝ፤
- የግል መከላከያ ቁሳቁስ፤ እና
- ከኤሌክትሪክ ጋር መስራት፡፡

አቅራቢው ስምምነት የተደረሰባቸውን ስራዎች ከመጀመሩ በፊት ተግባራዊነት ያላቸውን የኤሪክሰን የአቅራቢ የ OHS አሰራር ደረጃዎችን መለየት አለበት፡፡

የኤሪክሰን የ OHS አሰራር ደረጃዎች በማንኛውም ጊዜ በኤሪክሰን ሊሻሻሉ ይችላሉ፡፡ የኤሪክሰን የ OHS አሰራር ደረጃዎች ከለሳ ከተለቀቁበት እለት አንስቶ ሌላ  የፅሁፍ ስምምነት ከኤሪክሰን ጋር እስከ ሚደረግበት ጊዜ ድረስ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፣ ሌላኛው አቅራቢ የኤሪክሰን የ OHS አሰራር ደረጃዎች ላይ በአቅራቢው ስራውን በሚገባው ደረጃ የማድረስ ብቃት ላይ እክል የሚፈጥር ለውጥ በሚያይበት ጊዜ፤ ኤሪክሰን እና አቅራቢው በነዚህ ለውጦች አተገባበር ዘዴ፣ አንደምታ እና የጊዜ ገደብ ዙርያ መወያየት አለባቸው፡፡

# 4 የኤሪክሰን ልዩ የ OHS ደረጃዎች

ይህ ልዩ የስራ ቦታ ጤንነት እና ደህንነት (OHS) ደረጃ ለሁሉም የግንባታ፣ የመስክ ጥገና፣ የኔትዎርክ መልቀቂያ አገልግሎቶች እና ለሁሉም ይህ ሰነድ በውል ላይ ተያይዞ ለቀረበለት ኣቅራቢ ሁሉ ግዴታ ነው፡፡ ደረጃዎቹ ለሁሉም አቅራቢዎች ሚመከሩ ናቸው፡፡

# 5 የለውጥ መረጃ

ከከለሳ B ጀምሮ ያሉ ለውጦች፡-

- ለህግ የተጻፈ ጽሑፍ (2)